# ትብብር ከማን ጋር? ዓላማውና ልዕለ-ግቡስ?

## ኢትዮጵያን ለማዳንና ሕዝቧን ለመታደግ ኢትዮጵያዊ አስተሣሰብንና እምነትን ይጠይቃል!

*ከአያልሰው ደሴ፦ የግል አስተያየት ( ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፪ ሺ ፲ ዓ/ም)*

*ሠፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቶቹ መከበር ያደረገው የረጅም-ጊዜ መራር ትግል ሙሉ ምላሽን ባያገኝም፤ ትግሉ አልቆመም፤ አይቆምምም። በአገራችን ላይ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልጉ ኃይሎች ሁሉ የትብብር አስፈላጊነትን ሲሰብኩ መሰማቱ አዲስ ነገር አይደለም፤ የቆየና ለረጅም-ጊዜ በበርካታ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ወገኖች ብዙ አድካሚ ጥረቶች ያለማቋረጥ የተካሄደበት ጉዳይ እና ኢትዮጵያውያንም አጥብቀው የሚፈልጉትና የሚታገሉለት ቅዱስ ዓላማ ነው።*

*የዚኽ አጭር ጽሑፍ መነሻ የሆነኝ በቅርቡ በይፋ እየተወራለት ስላለውና በተለይም ከአገር-ውጭ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ማኅበረሰባችን መኻል የሞቀ ውይይትና ክርክር እያጫረ ስላለው የግንቦት ሰባት፣ የኦሮሞ ነፃ-አውጭ ግንባር (ኦነግ) እና የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር (ኦብነግ) አብሮ ለመሥራት አደረጉ የሚባለውን "ስምምነት" ተከትሎ እየተንፀባረቀ ያለው ሁኔታ ነው። በዚኽ ጉዳይ ላይ የፓልቶክ ውይይት መድረኮች ሠፊ ክርክሮች ያደርጋሉ ይባላል። እግዚአብሔር ይስጣቸውና ልሣኑ በዛብህ የተሰኙ አንድ ኢትዮጵያዊ ይኽንኑ በተመለከተ በኢትዮሚዲያ ላይ አንድ ጽሑፍ አስነብበውናል። በዓባይ ላይ ይገደባል በተባለው ግድብ ላይ ሲሰጥ እንደሚሰማው መላ-ቅጡ የጠፋ አስተያየት በዚኽ ጉዳይም እንዲሁ ሆኖ በማየቴ አዝኛለሁ። (በዓባዩ ጉዳይ በቅርብ እመለስበታለሁ።)*

*ከወዲኹ ግልጥ ማድረግ የምፈልገው አንደኛ ከነዚኽ ኃይሎች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት መደረግ የለበትም የሚል አቋም ባይኖረኝም ቅሉ (በሁለተኛው ክፍል ለማሣየት እንደ-ሞከርኩት) በተለይ የአንድነትና የዴሞክራሲ ኃይሉ በተዳከመበትና አንድ ላይ መቆም ባልቻለበት በአሁኑ ጊዜ ቅድሚያ የማይሰጠው ጉዳይ ነው። ሁለተኛ በዚኽ ሂደት ውስጥ ሙሉ ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ጥረት የሚያደርጉ አብዛኞቹ ወገኖች ለግል ጥቅማቸው ሣይሆን አገራቸው ኢትዮጵያን ከልባቸው ስለሚወዱና ወገናቸውን ከመለስ ዜናዊ አምባ-ገነን አገዛዝ ለማላቀቅ ካላቸው ጉጉት እንጂ ፀረ-ኢትዮጵያ ክፍሎችን ለመርዳትም ይሁን በኢትዮጵያ ላይ ለሚፈጸም ደባ እያወቁ ተባባሪ ለመሆን አስበው እንዳላደረጉት እምነቴ መሆኑን ነው። "የገሃነመ-እሣት መንገድ በወርቅ የተነጠፈ ነው" እንደሚባለው ግን በአገሪቱ ላይ ያለው ሁኔታ እንዲቀየር ያላቸው ጉጉትና ለሥርዓቱ ባለቤቶች (ለነ-መለስ ዜናዊ) ያላቸው ከፍተኛ ጥላቻ አሁን አብረዋቸው የተሠለፉ ኃይሎች በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ያላቸውን ከፍተኛ ጥላቻና አጥፊ አጀንዳ አጥርተው እንዳያዩ እይታቸውን እንዳደበዘዘባቸው ወይም ግርዶች እንደሆነባቸው ወይም እንበለ ተጨባጭና አስተማማኝ ምክንያት ቀለል አድርገው እንዲወስዱት እንዳደረጋቸው እገምታለሁ። ዞሮ-ዞሮ ግን ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ግምታቸው የተሣሣተና እርምጃቸውም ቆይቶ የሚያፀጽታቸው እንደሚሆን እገምታለሁ።*

*ከላይ በተጠቀሰው ርዕስ ሥር ከዚኽ በታች የማቀርበውን የግል አስተያየት አስተያየቱ ከቀረበበት መንፈስ ውጭ በመረዳት ወይም በተለየ መልክ በመተርጎም እንደ-ተለመደው በአገር አንድነት ዙሪያ የሚሰጥን በተለይም ፀረ-አንድነትም ይሁን የመገንጠል ዓላማን ባነገቡ ክፍሎች ላይ የሚሰነዘርን ቀጥተኛ አሣብ "በትምክኽተኝነት" ሊከሱና ደፈናዊ ወገዛን አልፎም ውርጅብኝ ለማውረድ የሚንደረደሩ ወገኖች እንደሚኖሩ አላጣሁትም። በተወሰነ ደረጃም ይሁን እንጂ አንዳንድ በኢትዮጵያ ስም የሚንቀሣቀሱና ከነዚኽ ኃይሎች ጋር በቅርበት የሚሠሩ ወገኖችም እንዲሁ በተነሣው ጉዳይ ፍሬ አሣብ ላይ ከማተኮርና ጭብጡን ተረድተው ጤናማ ውይይትና ካስፈለገም ይፋዊ ክርክር በማድረግ ፋንታ በነሱ ላይ የተዘመተ አልፎም "ትግላቸውን ለማደናቀፍ የተሸረበ ሴራ" አድርገው ሊያቀርቡ እንደሚደፍሩና እንደሚግደረደሩ አልጠራጠርም። መቸም ያ ዓይነት "አፍ-ማስዘጊያ" እኩይ ዘመቻ አዲስ ደራሽ ባይሆንም በተለይም ሕወሓት/ኢሕአዴግ አገራዊ ሥልጣን ላይ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ በነገሠው ከፋፋይ ፖለቲካዊ-ጎሠኝነት እንደ ልዩ ዘይቤ የተወሰደና ኢትዮጵያውያን አገርና ሕዝብን በሚያኽል ቁም-ነገር ላይ ሃቅን ይዘው ግልጥ ውይይትና ጤናማ ክርክር እንዳያደርጉ ሸብቦ የያዘና እውነተኛ አገር-አድን መፍትኄ እንዳይገኝ ግርዶሽ እንደሆነ አስባለሁ። ይኽ ኢትዮጵያውያን አንገብጋቢ በሆነው የአገራቸውና የወገናቸው ጉዳይ ላይ ገላቸውን ሰደው በነፃነት አሣባቸውን እንዳይሰጡ ሸብቦ የያዘና በተለይም አገር-ወዳዱንና ዴሞክራቱን ወገን "አንገት እንዲደፋ" ለማድረግ ለረጅም ጊዜ ተግባር ላይ የዋለ አነሁላይና ትጥቅ-አስፈቺ ዘዴ ነው። በበኩሌ ግን ያላስፈላጊ አዲስ አጀንዳ መሆኑና መባከን የሌለበት ጊዜ እንዲባክን ማድረጉ አንዳንድ ወገኖችን ሊያሣዝን ቢችልም፣ የጉዳዩ አሣሣቢነት በቀላሉ የማይታይ ስለሆነ ይኽ ዓይነት አካሄድ የሚኖረውን አሉታዊ ገፀ-ባኅሪ በመረጃ አስደግፌ በስፋት ለመቃኘት ዝግጁ ነኝ።*

ምንም አሣብ በነፃነት እንዳይንሸራሸር እንቅፋት መፍጠርና ያም በኅብረተሰቡ እንደ-መደበኛ ነገር በለሆሣስና በአርምሞ መታየትና መወሰድ ከተለመደ ለአፈ-ጮሌ ወናፎች መረማመጃ ከመሆንና ለአምባ-ገነናዊ አፋኝ የአገዛዝ ሥርዓት ሁኔታን ማመቻቸት መሆኑ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ በጣም የሚገርመኝ ይኸንን ዓይን-ያወጣ የግርንቢጥ ስሌት አገር-ወዳዱና ዴሞክራቱ ወገን በአብዛኛው "አክራሪ፣ ትምክኸተኛ፣ ወዘተ.." ላለ-መባል በለዘብተኝነት "ተቀብሎ" መቀጠሉና የብዙኃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምፅ በአናሣ ጮሌዎች እንዲታፈን መፈቀዱ ነው፡፡ የዚኸ አስተሣሰብ ሰለባ ተሆኖ ግን አገርን ማዳንም ይሁን ነፃ ኅብረተሰብ ለመመሥረት እንደማይቻል ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል እላለሁ፡፡ ስለሆነም ይኸ የተዛባ አመለካከት መቆም አለበት እላለሁ፡፡

በተወሰነ ደረጃም ይሁን እንጂ ከተማሪው እንቅስቃሴ ጀምሮ በ"ብሔር/ብሔረሰብ" መብት ስም እስከ-መገንጠል ድረስ ፅንፈኛ አመለካከቶች ሲንሸራሸሩ ጉዳዩን እንደ-"ትክክለኛና ተገቢ" አቋም ከማስተናገድ ጨርሶ እስከ-መደገፍ የደረሱ አመለካከቶች፣ ቢያንስ ግን ይፋዊ ተቃውሞ አለማሰማት፣ በአንዳንዶች ዘንድ ደግሞ ልክ እጅጌ-ጉርድ ካኪ እንደ-መልበስ "የተራማጅነት" ምልክት ተደርጎ የተወሰደውን ያኽል፤ የዜጎችን እኩልነትና መብት መከበርና የኢትዮጵያ አንድነት ባልተነጣጠለ መልኩ እንዲታዩ አበክረው የተከራከሩ ጥቂቶችን በ"አክራሪነትና በትምክኸተኝነት" አልፎም እንደ "ኋላ-ቀርና አድኃሪ" የተቆጠሩበት ጊዜ እንደ-ነበር አይዘነጋም፡፡ ያም ሆኖ ግን ከዚያ ታጋይ ትውልድ በርካታ ከሆኑ እጅግ አኩሪ ገፅታዎች ውስጥ አንዱ ከየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ይሁኑ ከየት ኢትዮጵያውያንን በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ያየ እና ፖለቲካዊ-ብሔረሰበኝነትን/ጎሠኝነትን ስሌቱና መመዘኛው ያላደረገ ሠፊ አስተሣሰብ ላይ የተመሠረተ አገር-አቀፍ እንቅስቃሴ መሆኑ ነበር፡፡ ምንም እንኳን ያኔም ቢሆን ከአጠቃላዩ ይልቅ ወደየጓዳቸው ያተኮሩ ወገኖች ባይጠፉም፣ እነዚያ ክፍሎች "የእኛ" ብለው ከሚቆጥሩት የኅብረተሰብ ክፍል ውስጥ በአባልነት ካቀፏቸው ይበልጥ በኢሕአፓ ይሁን በመኢሶን እንዲሁም በሌሎች ተራማጅና አገር-አቀፍ ድርጅቶች ውስጥ የነበሩት ታጋዮች ቁጥር በእጅጉ አብላጫ እንደ-ነበረው ግልጥ ነው፡፡ ያ ቋንቋ፣ ብሔረሰብ/ጎሣ፣ ሐይማኖትና አካባቢ ሣይለዩ በጅምላ የጨቆኑ ሥርዓቶችን በጋራ ትግል ለማስወገድና የጋራ መጻዒ-ዕድልን በጋራ መተለምና መወሰን ይቻላል ከሚል ጠንካራ እምነት ላይ ተመሥርቶ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ ለማስገኘት የቆመ አብዮተኛ ትውልድ አሠላለፉ ቋንቋ፣ ብሔረሰብ/ጎሣ፣ ሐይማኖት፣ ፆታና አካባቢ-ዘለል ስለ-ነበር ኢትዮጵያዊነትን በትክክል ያንፀባረቀና የአንድነት ስሜትና የቁርጠኝነት መግለጫ እንደ-ነበር በኩራት ሊዘከር ይገባዋል፡፡

ኅብረተሰብን ለመለወጥ የተነሣ ማንኛውም ዜጋ ከሁሉ በፊት እራሱን በእምነት መቀየር እንዳለበት የታወቀ ነው፡፡ በዚያ በጥቅሉ 'የተማሪው እንቅስቃሴ' እየተባለ በተጠራው የአብዮት ወቅት ለሁሉም ኢትዮጵያዊ የወልና የግለሰብ እኩልነትና መብቶች መከበር መሠረታዊ የአስተሣሰብ ለውጥ በራሣቸው ላይ ያደረጉና ለሕዝብ ዓላማዎች ከልብ የተሰለፉ፣ ምትክ-የሌላት ሕይዎታቸውን በፈቃዳቸው አሣልፈው የሰጡ ኢትዮጵያውያን ሥፍር-ቀጥር አልነበራቸውም፡፡ የኤርትራ ጉዳይ በሰላም እንዲፈታ፣ "የብሔር/ብሔረሰቦች" እኩልነት እንዲረጋገጥ፣ መሬት-ላራሹ እንዲሆን፣ የሠራተኛው መብት እንዲከበር፣ ኋላ-ቀር ሥርዓት እንዲወገድ፣ ወዘተ.. ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ከጮሁ፣ አምርረው ከታገሉና ሕይዎታቸውን ከገበሩ እልፍ-አእላፍ ወጣቶች ውስጥ በእጅጉ የሚበልጡት አንዳንዶች "መደባቸውን የሸጡ" ብለው የሚጠቅሷቸውና "ጨቋኝና በዝባዥ" ከተባለው አማርኛ ተናጋሪው ኅብረተሰብ የወጡ እንደሆነ አሌ የሚባል አይመስለኝም፡፡ አዎን፤ አንዳንድ ጊዜ "መኖር-ደግ ነው" የሚለው አባባል ለአንዳንዶች ትርጉም-የለሽ ሆኖ ቢገኝም፣ ትላንት በዚያ ቀውጢ "የተራማጅ" እንቅስቃሴ ውስጥ ሠፊ-አስተሣሰብ እንዳላቸው የሚታመኑ፣ ከሠፊም ሠፊ "ዓለም-አቀፋዊ" ነን ብለው የተመፃደቁ መኻል፣ እንዲያውም በልዩ ልዩ አመራር ቦታዎች ላይ የነበሩ ታጋዮች ሣይቀሩ "በእብዶች መንደር አብረህ እበድ" ዓይነት ብኂል እነሆ በዘመነ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ ያንን "የተራማጅነትና የዓለም-አቀፋዊነት" ሠፊን ካባ ውልቅ አድርገው በመጣል ወደ-ኋላ ሄደው ጠባብ ጎጠኛና ጎሠኛ ጥብቆአቸውን ሲያጠልቁ በትዝብት የተመለከትናቸውም አልጠፉም፡፡

የሆነ-ሆኖ፤ እዚኸ ላይ ለወገን ኢትዮጵያውያን ለማሣሰብ የምወደው አገራዊ አንድነት እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን ሁለንተናዊ መብቶችና እውነተኛ እኩልነት መከበር ሣይነጣጠሉ ተጣምረው የሚታዩ ባሕረ-አሣቦች እንጂ አንዱ ለሌላው መስዋዕት የሚሆንም ሆነ አብረው የማይሄዱና ተፃራሪ እምነቶች እንዳልሆኑ ነው፡፡ የትግል ታሪካችንም አንገቱን ቀና አድርጎ በኩራት የሚመሰክረው ሃቅ ያንኑ ነው፡፡ የዚያ ትውልድ ግርፍ የሆነ ሁሉ እንደሚረዳው ኢትዮጵያውያን አይከፍሉ መስዋዕትነት የከፈሉት ዜጎች ከኋላ-ቀርና በዝባዥ ሥርዓት ተላቅቀው አድልዖ በሌለበት ፍትኃዊ ሥርዓት ሙሉ መብቶቻቸው ተከብረውላቸው በአገራቸው ላይ ኮርተው የሚኖሩበት ሁኔታ እውን እንዲሆን እንጂ አንዱ የበላይ ሌላው የበታችና የእንጀራ-ልጅ ሆኖ በሚታይበት ጨርሶ ተቀባይነት የሌለውና የተዛባ የኅብረተሰብ ስሪት ሥር እንዲወድቅ ወይም የጭቆና አዙሪት በሌሎች

ተዋንያን በከፋ መልኩ እንዲቀጥል አልነበረም፣ አይደለምም፡፡ ለሕዝባችን ኋላ-መቅረትም ይሁን መጨቆን የኢትዮጵያ አንድነት ምክንያትም ሆነ ተጠያቂ እንዳልሆነ ደግሞ ግልጥ ሊሆን ይገባል፡፡

እየጠበበና ይበልጥ እየተቀራረበ በሄደ የዓለም ሁኔታ፣ በተለይም የዜጎችን እኩልነት የሚያረጋግጥ ሥርዓት እውን እንዲሆን የጋራ ትግል በቀጣይነት እየተካሄደ ባለበት አገር የመገንጠል ጥያቄ ማንሣቱ አንድም በዚኽ የጋራ ጥረት ውስጥ ክቡር ሕይዎታቸውን የገበሩና እየገበሩ ያሉ ኢትዮጵያውያን (እነኝኽ ክፍሎች "ቆመንለታል፣ እንወክለዋለን" ከሚሉት የኅብረተሰብ ክፍል የወጡትን ሚሊዮኖች ጭምር) በእጅጉ ዝቅ አድርጎ ያየ እና በመስዋዕትነታቸው የተሣለቀ አለያም የብዙኃኑን ጥቅም ለማስከበር ሣይሆን የጥቂት "ልኂቃንን" የሥልጣን ጥም ለማርካት የሚደረግ ግብዝ ጥረት ስለሚሆን ጥያቄአቸው ከእኩልነትና ከፍትኅ ጋር ግንኙነት አለው ማለት ይከብዳል፡፡

እንክርዳድ ዘርቶ ስንዴ ማምረት እንደማይቻል ሁሉ የኢትዮጵያ ሠፊ ሕዝብ ጥቅም ማስጠበቅ፣ እኩልነትና አገራዊ አንድነት ማስከበር የሚቻለው ኢትዮጵያዊ አመለካከትና እምነት ባላቸው ወገኖች እንጂ አምርረው በሚጠሏትና ሊቆራርጧት በሚታገሏት ክፍሎች ሊሆን እንደማይችል ደግሞ በተገቢ ሊታወቅ ይገባል፡፡

**በሁለት ተመሣሣይ ከፋፋይ የፖለቲካ እምነት አራማጅ አናሣ ኃይሎች መኻል ከሁለት አቅማጣጫዎች የተወጠረው፣ አጣብቂኝ ውስጥ የወደቀውና መቀጣጠቢያ የሆነው ኢትዮጵያዊነት!**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ልዕለ-ግብ የአምባ-ገነን ሥርዓቶችን አዙሪት ለመስበርና የዜጎች እኩልነት በተግባር የሚረጋገጥበት፣ የራሱን ዕድል በራሱ የሚወስንበት የለተሻለ ዴሞክራሲያዊና ፍትኃዊ ሥርዓት ባለቤት እንዲሆን እና አገራዊ አንድነታችን የማይናወጥ መሠረቱ እንዲጠና መሆኑ ይታወቃል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ላይ ያለው ኢሕአዴጋዊ ከፋፋይ የአፈና አገዛዝ መወገድ የሚኖርበትም ወደዚያ ልዕለ-ግብ ለማምራት እንቅፋት ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ ይሁንናም ይኽ የሕዝባችን የእኩልነትና የፍትኅ ትግል በሁለት ተመሣሣይነት ባላቸው አሉታዊ አናሣ ኃይሎች መኻል አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ይገኛል፡፡ ሕዝባችንን ከዚኽ አጣብቂኝ ታግሎ በማታገል መንጥቆ እንዲያወጣው ታሪካዊ ኃላፊነት ያለበት አገር-ወዳዱና ዴሞክራቱ ኃይል ደግሞ ቆም-ብሎ እራሱን ፈትሾ እምነቱን ባለማሾሩና ሠልፉን ባለማስተካከሉ፣ ያለውን እምቅ አቅሙንም በቅጡ ባለመረዳቱና ባለመጠቀሙ፣ ሕዝባዊ ዓላማው እንዲበረዝ፣ ትግሉም በነኝኽ ኃይሎች ተጠልፎና ታግቶ እንዳልሆነ እንዲሆን በማድረግ እራሱም ተልሞስሙሶ ትግሉን አልሞስሙሶቷል ማለት ይቻላል፡፡ እነኝኽ ኃይሎች ትግሉን ከሁለት አቅጣጫ ቀስፈው ስለያዙትም አገር-ወዳዱና ዴሞክራቱ ክፍልም የዚኹ ሰለባ ቀላል ኢላማ ሆኖ እየባዘነ ይገኛል፡፡ በመኻል እንበለ-አገራዊ እምነት አገራዊ ሥልጣን የያዘው ሕወሓት፣ "በተቃማዊው" ጎራ እንደ-ኦነግ የመሰሉ ከአገሪቱ ምልዓተ-ሕዝብ ለተወሰነው ክፍል ብቻ "ቆመናል" ባሉ ኃይሎች ከሁለት አቅጣጫ ተመሣሣይ የፖለቲካ ፍልሥፍንና በሚከተሉ፣ አግላይና ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች እኩል ባልቆሙ ወገንተኛና ጎሠኛ ቡድኖች መሣሣብ ተወጥሮ እና እንደ ድፎ ዳቦ "ከላይ እሣት ከታች እሣት" ሆኖበት በነዚኽ አንድም-ሁለትም በሆኑ ሁለት አናሣ ኃይሎች መኻል ተቀስፎ ተይዞ አንድነቱን አጥቶና የጋራ ጥቅሙን በጋራ ትግሉ እንዳያስከብር የጉሮሮ-አጥንት ሆነውበት ይገኛል፡፡

ለአወንታዊ ለውጥ በሚታገሉ የኢትዮጵያ አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይሎች ይዞታና የኃይል-አሠላለፍ ላይ ያየኋቸውን (ያለፍኩባቸውን ጭምር) ችግሮችና ይበጃል የምለውን አካሄድ በተመለከተ ያለፉ የጋራ ትግል ጥረቶችን ሂደት ለወደ-ፊቱ ቀጣይ የጋራ ትግል አንዳንድ መረጃዎችን በማቅረብ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ቢጠቅም ከሚል በተከታታይ በማቀርባቸው ዘገባዎች ከክፍል ሃያ-አምስት ጀምሮ የቀረበ ቢሆንም፤ በአሁኑ ጊዜ ቀደም-ሲል በተጠቀሱት ቡድኖች መኻል እየተካሄደ ስላለውና በበኩሌ 'ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ - ዙር ሁለት ' AFD II' ፣ ብዬ የምጠራው ይኽ ኩኔት በጋራ ትግሉ እና በሕዝባችንና በአገራችን መጻዒ-ዕድል ላይ ስለሚኖረው አሉታዊ ገፅታ አስተያየት መስጠት የግድ ሆኗል፡፡

ይኽ በአንድ በኩል ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት፣ እኩልነትና አንድነት ቆመናል በሚሉና በሌላ በኩል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንደ-ዋና ጠላታቸው ቆጥረው ከዘመቱ ኃይሎች ጋር የሚካሄድ "ትብብር" ብዙዎች ትርጉም ሊያገኙለት የተቸገሩ መሆኑ ቢታወቅም፣ በባለ-ጉዳዮቹ ዘንድ ግን "በመቻቻል" መርኅ ላይ የተመሠረተ "ደፋር" እና "የትግሉን ጊዜ የሚያሳጥር ወሳኝ" እርምጃ እንደ-ሆነ፣ አልፎም በአንዳንድ አፍቃሪ-ሸዓብያ "ፀሐፊዎች" "ወያኔ በጣም የሚፈራው ብቸኛ ኃይል" ተደርጎ ሲቀነቀን ታዝቤአለሁ፡፡ ይኽንን የተዛባ አካሄድ "የመቻቻል" ፖለቲካ ሊሉት ቢቃጡም ከሰባ-ሦስት ዓ/ም ጀምሮ ልዩ ልዩ ድርጅቶች ተቻችለው በግንባርና በጋራ አልፎም በውኅደት ባደረጓቸው ጥረቶች ቀጥተኛ ተሣታፊ የመሆን ዕድል የነበረኝና አሁንም የተለያዩ አቋሞች ካሏቸው ድርጅቶች ጋር አብሬ እየሠራሁ ያለሁ በመሆኔ፣ 'መቻቻል' በቁንፅሉ ተወስዶ ወይም በሌጣው

ሣይሆን ከማንና በምን ዓላማዎች ዙሪያ እንደሆነ የጠራ ግንዛቤ ያስፈልገዋል የሚል እምነት አለኝ:: የሆነ-ሆኖ በኔ በኩል መቻቻል አጥፊና-ጠፊ በሆኑ፣ ጎልውናን ከሚፈታተን/ኑና ማንነትን ከማይቀበል/ሉ ወይም ወደ-ተለየ መዳረሻ በተቃራኒው ከሚሄድ/ዱ ጋር ሣይሆን ከዚያ በመለስ ያሉ የግንዛቤም ይሁን የአመለካከት ልዩነቶችን አዋውጦና ተከባብሮ በተለያየ መንገድና ዘዴም ይሁን እንጂ በአንድ አቅጣጫ ከሚጓዝ/ዙ ክፍል/ክፍሎች ጋር ቢያንስ ግን ያ የሥርዓት ለውጥ እውን እንዲሆን በሚፈለግበት ቦታ/አገር አንድነት ላይ ምንም ዓይነት ጥያቄ የሌለበት ተመሣሣይ እምነትና አቋም መኖርን የግድ በሚል ላይ ቆሞ ሚደረግ የዝምድና ወይም የግንኙነት ሂደት ነው:: ከሁሉም በላይ ደግሞ ያ ዓይነት "ትብብር" የሚደረግበትን አጠቃላይ የኃይል አሠላለፍ፣ ሁኔታና ወቅቱን በጥሞና መመርመሩ  በእጅጉ አስፈላጊ ይሆናል:: ለምን ቢሉ ወንዝ መሻገር ያቃተውና የተቸገረው መርዘኛ እባብ ዘዴኛ ሆኖ እንዲያሸግረው በመቅለስለስ የተማፀነውን ሰውና የለዘበ አቀራረቡን ተማምኖ ተሸክሞ ወንዙን ያሻገረው ያ የዋኅ ሰው መኻል በኋላ የሆነውን ማስተዋሉ ተገቢ ነውና::

እርግጥ ነው አቀንቃኞቹ እንደሚሉትም ይኸ እርምጃ "ደፋር" ነው:: ደፋርነትቱ ግን በሚነገርለት "የፖለቲካ ብስለትን" የሚያሣይ ሆኖ ወይም ትግሉን የሚጠቅም አዲስ ግኝት ሆኖ ሣይሆን በመስክ ላይ ያለውን ሃቅ ያላገናዘበ፣ ራቅ-አድርጎ ያላየ፣ ታሪክን የዘነጋ፣ የድርጅቶቹን መሠረታዊ ተፈጥሮአዊ ባኅሪና ማንነት ያላስተባቃ፣ ኢትዮጵያዊ ብሔራዊ ስሜትን፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ አንድነትና ለአገራዊ አንድነትና ለዴሞክራሲ የሚደረገውን የጋራ ትግል ዓይን የጠነቆለ፣ ኢትዮጵያዊ ማንነትን፣ አገር-ወዳድነት፣ ውበቱንና ኃይሉን በእጅጉ የናቀና የተዛበተ እርምጃ በመሆኑ ነው:: ትግሉ የግለሰቦችና የቡድኖች በግለሰቦችና ቡድኖች ላይ ሣይሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቶች መከበርና ለዴሞክራሲ ለሚያደርገው ትግል ጠርና ቀበኛ በሆኑት እነዚያ ክፍሎች በሚከተሉት ርዕዮትና በሚያራምዱት ፍልስፍና ላይ ሊሆን ይገባል:: የመለስ ዜናዊን አገዛዝ ኢትዮጵያውያን የማይቀበሉት ብቻ ሣይሆን የሚያወግዙትና ባላቸው አቅምና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ አምርረው የሚታገሉት በተግባር እየተገለጠ ካለው የዞረበት፣ ኋላ-ቀርና ከፋፋይ፣ ጨቋኝና አፋኝ፣ አግላይና ለሁሉም እኩል ያልቆመ ጠባብ ቡድነኛና አድልያኣዊ ሥርዓት በመሆኑ ነው:: አገዛዙ ይኸንን ገፀ-ባኅሪ የተላበሰው ደግሞ ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ ለማሣሰብ እንደ-ሞከርኩት፣ ከሚከተሉት የፖለቲካ ፍልሥፍናና በዚሁ ላይ ከተመሠረተው አደረጃጀታቸው እንጂ ከትግራይ ስለ-ተወለዱ ወይም ግለ-ሰቦቹ እነ አቶ መለስ ዜናዊ ስለሆኑ አይደለም:: የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚያደርገው የፍትኅና፣ የአርነትና የአንድነት ትግል እነዚኸን እሴቶች ከሚፃረሩ አፋኝ አምባ-ገነን ገዥዎችና አራማጆች ጋር ብቻ ሣይሆን ለነዚያ ፀረ-ሕዝብ እርምጃዎቻቸው ቀጥተኛ ተጠያቂ ከሆኑ የአገዛዙ ሥርዓት ከተመሠረተባቸውና ከቆመባቸው የፖለቲካ ፍልሥፍናና ከሚከተሉት እምነት ጋር ስለሆነ ትብብር የሚፈጠረው እነዚኸን ከሚያራምዱ ክፍሎች ጋር ከሆነ ውጤቱ ቢያንስ "ውሃ-ቅዳ ውሃ-መልስ" ዓይነት ትርጉም የለሽ ይሆናል:: ችግሩ ግን ትርጉም-የለሽ ብቻ አይደለም፤  ከንቱና አደገኛም ነው:: ዞሮ-ዞሮ የዚኽ አሁን የተያዘው ዓይነት "አብሮ መሥራት/መተባበር" ለእነኝኸ ኃይሎች ያጠራቸውን አየር ከመስጠትና ሕይዎት-አድን እስትንፋስ ከመሆን፣ እነሱን ከማጠናከርና ለሚታገሉበት ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ኢትዮጵያዊነት ዓላማና ግብ-አስጨባጭ ትልም (ስትራተጂ) ቀጥተኛ አስተዋፅዖ ከማድረግ የተለዬ ውጤት አይኖረውም:: ስለሆነም እርምጃው 'የጅል ዱላ አቀባይ' ወይም 'የዕብድ ገላጋይ ጩቤ ያቀብላል' ዓይነት ይሆናል:: በመሠረቱ ማንም ቡድን (ክፍል) ኢትዮጵያዊ አይደለሁም፣ የተወሰነውን የአገሪቱን ቀጠና እገነጥላለሁ ብሎ ሲነሣ ሌላ ሣይሆን ቀጥታ ትርጉሙ በአገሪቱና በኢትዮጵያዊነት ላይ ጦርነት አወጀ ማለት እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል::

ይኸንን "አዲስ ትብብር" ከሚያምዱና ከሚደግፉ አካባቢ በተደጋጋሚ የሚሰጡ ልዩ ልዩ የማሳመኛ ምክንያቶች ይሰነዘራሉ:: ከነዚኽ ውስጥ፤ ሀ) "ወያኔን ለመጣል ከማንም ጋር መተባበር ይገባል"፤ ለ) "ወያኔ የሚገባው ቋንቋ ኃይል ስለሆነ በተለይ ከታጠቁ ክፍሎች ጋር ተባብሮ መሥራቱ የአገዛዙን ዕድሜ ለማሣጠር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው"፤ ሐ) "ትጥቅ አንስተው የሚታገሉ ኃይሎችን ምንም ጥያቄ ያንሱ ምን ቀርቦ ማነጋገሩና አብሮ መሥራቱ የበለጠ አክራሪ እንዳይሆኑ ይረዳል"፤ መ) "እነዚኸ ኃይሎች ጋር ከአሁኑ አብሮ መሥራት ካልተጀመረና አብረናቸው እንደምንሠራ ካላረጋገጥንላቸው እንደገፋናቸው ይቆጠራል፣ በኋላም ወያኔ ሲወገድ ማቅረብ አይቻልም"፤ ሠ) "ከነሱ ጋር አብሮ መታገሉ አገር-አቀፍ ብሔራዊ መግባባት እንዲኖርና ዴሞክራሲ እንዲያብብ የተሻለ ሁኔታን ይፈጥራል"፤ ረ) "ከነዝኸ ኃይሎች ጋር መሥራት አለ-መፈለግ ወደ-ፊት ያዬ ሣይሆን ወደ-ኋላ ያየ ነው:: ከአሁን በፊት ስለ-ተደረጉ ነገሮች የምንነጋገርበት ጊዜ አሁን አይደለም፣ ይኸንን የሚተቹ የተሻለ አማራጭ ማቅረብ ያልቻሉ ክፍሎች ናቸው"፤ ሰ) "ይኸ እርምጃ ደፋር፣ አግላይነት የሌለውና አርቆ-ያየ ነው"፤ አልፎም "ቀስ-በቀስ መቀራረብ ከተፈጠረ እኛ በምናስበው መልክ ችግራቸውን በኢትዮጵያ አገራዊ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲፈታ ለማድረግ ቃል አስገብተናቸዋል"፣ወዘተ.. የሚሉ ይገኙበታል:: እስኪ እያንዳንዳቸውን እንይ::

***ይቀጥላል...***